# የዮፍታሔ ትዝታ



ኤውሮጳ ተባብሮ ጎዋህ ሲናፈስ፣
ኣሜሪካም እንዴሁ ጨረቃ ሲደርስ፣
መስኮብም ጠንክሮ በባሕር፣ በየብስ፣
ነጭ ዘር ወንድ ልጁን ሲያስተምር ፈረስ፣
ቻይናም ሴቷን ልጁን ሲያስትምራት ተኩስ፣
ምነዋ ጥቁር ዘር ኣቃተው ማረስ?

ምኒልክ ይነሳ ከኣምበሳው ጎፈሬ፣
ኬንያታንም ላውጣው መቃብር ቆፍሬ፣
ሉሙምባም ይነሳ ኣሁኑኑ፣ዛሬ
ኑኩርማም እያለ፤ "ሃገሬ፣ ሃገሬ!"

ማንዴላም እያለ፤ "ወገኖቼ፣ ዘሬ
በርቱ ተበራቱ እንዳልቀር ኣፍሬ!"

ኣፍሪካ ተባብራ ካልረገጠች እርካብ
ጥቁር ዘር ለወትሮው እምቧይ ካብ፣ እምቧይ ካብ!

## የዮፍታሔ ትዝታ - ፪ኛ





የኣፍሪካ ልጆች ኬንያታ፣ ኑኩርማ፣ ሉሙምባ፣
ጀግና ሰው ተወልዷል የኣፍሪካ ኣምባ...
እምቧይ ካብ ኣይደለም! ሁሉም ተፈጽሟል፣
ኣባይን ሲደፍር ሕልሙ ክሱት ሆኗል!

ምኒልክ ዓድዋ ላይ የተከለው ዘር
በመለስ ዜናዊ ተከፈተ በር
የሃፄ ዮሃንስ፣ የኣሉላ ልጅ
ግሩም ጥበበኛ፣ ዕጹብ ባለእጅ!
ከዓድዋ ገሰገሰ፣
ለፍሬ ደረሰ!
የኣፍሪካ ኣንበሳ ለኣፍሪካ ቆሟል፣
ተሟግቷል፣ ረትቷል፣ ኣዲስ ፈር ከፍቷል!



በሞያ፣ በተግባር፣ ዕድገቱ ተመርጦ
ወደፊት መገስገስ ያንን እርካብ ረግጦ...
ባሰመረው መስመር፣ በተለመው ትልም
ኣፍሪካ ተባብሮ ይቀጥል ያ ሕልም!

ገ/ኢ. ጐርፉ።